# አማራ ትግሬና አህያ (አድጊ)

አህያ የሚል ስድብ ከመቸ ጊዜ ጀምሮ አገልግሎት ላይ እንደዋለ ማወቅ ባይቻልም እንደሌሎቹ ክፉ የዐመፃ ሥራዎች ሁሉ ከሰው ልጅ ዕድሜ ያልተናነሰ ዘመን ሊኖረው እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ወደ ሀገራችን ስንመጣ "አህያ" የሚለው የስድብ ቃል በግልጽ በታሪክ ተመዝግቦ እንደምናገኘው የአንድ ብሔረሰብን አባላት ለመስደቢያነት ሲያገለግል እረጅም የሚባል ዕድሜ የለውም፡፡ ከመቶ ስድሳ ዓመታት አይበልጠውም፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡-

አባ ገብረሐናን የማያውቅ ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡ አባ ገብረሐና ተረበኛና ቧልተኛ ሰው ነበሩ፡፡ ቧልተኝነታቸው ሰዎችን ለሚያስቀይም ለሚያስከፋ ክፉ የቃላት አጠቃቀም (ዳኅፀ-ልሳን) ዳረጓቸው ነበር፡፡ አባ ገብረሐና ያን ያህል ታላቅ ሊቅ እና የሃይማኖት አባት የነበሩ ስለነበሩ እንዲህ ዓይነት ስሕተት ያውም በተደጋጋሚ ይሠራሉ ተብሎ ጨርሶ አይታሰብም እይጠበቅምም ነበር፡፡ ነገር ግን እነኛን ተደጋጋሚ ስሕተቶች ሆን ብለው ይሠሩ በነበሩበት ወቅት በጣም ያበዙት ስለነበረ ጤነኛ መሆናቸው እንኳን አጠራጣሪ የነበረና እንኳንና በእነ ሐድጎ የሃይማኖት መሠረት በሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ሳይቀር ሲያፌዙና ሲሳለቁ በወቅቱ ቅንጣት ታክል እንኳን የማይሰቀጥጣቸው ሰው ነበሩ፡፡

ታሪኩ እረጅም ስለሆነ ትተነው አባ ገብረሐና እራሳቸው በፈጠሩት መዘናጋት ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆነ ምክንያት ምንኩስናቸው በመፍረሱ በእግዚአብሔር አኩርፈው እሱን የተበቀሉት መስሏቸውም ይሁን ተስፋ ቆርጠው አይታወቅም ቅዱስ ቃሉን መዘባበቻ አድርገውት ነበር፡፡ የኋላ ኋላ ግን መድኃኔዓለም ሲታደጋቸው ልባቸውን መለሰላቸውና እጅግ በመጸጸታቸው በንስሐ ሕይወት ውስጥ እንዳሉ አርምሞ ይዘው (በምነና ሕይዎት ያለ ሰው ከሚያደርጋቸው የተጋድሎ ዓይነቶች አንዱ ሲሆን ትርጉሙም ከማንኛውም ሰው ጋር ምንም አለመነጋገር ዝምታ ማለት ነው) ከሁሉም ሰው ጋራ የማይነጋገሩ ስለነበሩ ዘመዶቻቸው አባ ገብረሐናን ጋኔን ልሳናቸውን ዘግቶት ነው ብለው ጸበል የተባለበት ቦታ ሁሉ እያዞሩ ብዙ ያንገላቷቸው ነበር፣ ከስንት ቀን አንድ ጊዜ ለቁመተ ሥጋ ታክል ጥቂት በመቅመስ ብቻም ሰውነታቸውን በመቅጣትና በማድከም ቅዱሳት መጻሕፍትን ከፊታቸው ደርድረው ድንጋይ እየተሸከሙ አብዝተው በመስገድ መዘባበቻ አድርጌያችኋለሁና ይቅር በሉኝ! በማለትና ሌሎች የመሳሰሉትን መንፈሳዊ ተጋድሎ ሲፈጽሙ ቆይተው በመጨረሻ ከቸሩ አምላካቸው ለሠሩት ሁሉ ኃጢአት ሥርዬት ከማግኘታቸውም በላይ በቅተው (ከቅድስና ደረጃ ደርሰው) እንዳረፉ ታሪካቸውን በቅርብ ከሚያውቁ አረጋዊያን ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን መረዳት ይቻላል፡፡

ለመሆኑ ግን አባ ገብረሐና ከሐድጎ ጋር የነበራቸው ግጭት ምን ነበር? ብትሉ ባጭሩ የሚከተለውን ይመስላል፡- ብላታ ሐድጎ ማለት የዐፄ ቴዎድሮስ ታማኝና ትጉ አገልጋያቸው የነበረ የትግሬ ተወላጅ ነው፡፡ አባ ገብረሐና ታዲያ የሐድጎን መጠሪያ ስም እያጣመሙ የዘሩንም ሥያሜ ወደ እማርኛ በመተርጎም ሐድጎ (አህዮ)፣ ትግሬ (መረገጫ፣ ተረጋጭ) እያሉ እያበገኑ ቢያስቸግሩት

““““ በነገራችን ላይ ይሄንን የአባ ገብረሐናንና የሐድጎን ታሪክ የጻፉ ሰዎች አባ ገብረሐና ሐድጎንና ስሙን በተመለከተ የተናገሩትን ብቻ እንጅ የዘሩን ሥያሜ በተመለከተ “ትግሬ መረገጫ ተረጋጭ” እያሉም ያበግኑት እንደነበር እስከማውቀው ድረስ አንድም ሰው እንኳ እንደጻፈ ሰምቸና ዓይቸ አላውቅም። በእርግጥ ምክንያት ሊኖራቸው ይችላል። እኔም እንደነሱው ሁሉ ይህችን “ትግሬ መረገጫ ተረጋጭ” የምትለዋን ነገር ለመዝለል የሚያበቃ ወይም የሚያስገድድ ምክንያት ሳይኖረኝ ቀርቶ እልነበረም። ነገር ግን “ታሪክ ታሪክ ነው! በምንም ምክንያት ቢሆን መስተካከል ወይም መቆነጻጸል (ኤዲት መደረግ) አይኖርበትም! አይገባምም። ይህ ከተደረገ ታሪክነቱ ይቀርና የሰዎች ተረት ይሆናል” የሚ

የታሪክ ጥናት ሞያ መርሕ ወይም መመሪያ **(principle)** ለመጠበቅና ይሄ መርሕም መጠበቅ አለበት ብዬ በጽኑ ስለማምንም እንጅ ስለ እውነት ይሄንን ጉዳይ መጻፍ ፈልጌ አልነበረም። ለማንኛውም አባ ገብረ ሐና እንዲያ እያሉ ሐድጎንና ወገኖቹን ያቆስሉ ነበር።

አሁን በዘመናችን ይሄ የሚያንገበግባቸው የእግር እሳት የሆነባቸው የሐድጎ ወገኖች ትግሮች (በእርግጥም እንደ ሰው ሊሰማቸውም ይገባል) ቢቸግራቸው በተለይ ከሁለት ዐሥርተ ዓመታት ወዲህ ትግሬ የሚለውን ቃል ትርጉም አባ ገብረሐና ከሚሉት ከዚያ ትርጉሙ ለማራቅ ቃሉን ትግራዋይ ወደሚል ቃል ቀይረው ይሄንንም ቃል ለማስለመድ እየተጣጣሩ ይገኛሉ። ይሁን እንጅ ሥርዎ ቃሉን አልለቀቀምና አልሸሹም ዞር አሉ ነው የሆነው እንጅ ሌላ ትርጉም አላመጡም ””””

ለማንኛውም አባ ገብረሐና ሐድጎን እንዲህ እያሉ አጣመው እየተረጎሙና እየመሰሉ ቢያስቸግሩት ለዐፄ ቴዎድሮስ ከሶ አቀረባቸው። አባ ገብረሐና ግን “እኔ ምን አደረኩ? ወላጆቹ ባወጡለት ስምና በማንነቱ በግብሩ ነው የጠራሁት። መተርጎሜ ከሆነ መተርጎም እኮ ሞያዬ ነው ጃንሆይ!” እያሉ ሊታረሙ ስላልቻሉ ሐድጎ ጨለማን ተገን አድርጎ አሸምቆና አድብቶ ማንነቱን ሰውሮ ሰዋራ ቦታ ጠብቆ ክፉኛ ደበደባቸው።

አባ ገብረሐናም ክፉኛ ተጎድተው ነበርና ለአልጋ በቁ። ታዲያ ሰው ሁሉ እየሔደ ሲጠይቃቸው ሐድጎም ነገሩን እንደማያውቅ ሰው ጨዋ ጠያቂ መስሎ ሊጠይቃቸው ወደ ቤታቸው ሔደና “አባ ገብረሐና እግዚአብሔር ይማርዎት! ምን አገኘዎት ከቶ?” ሲል በማስተዛዘን ጠየቀ። እሳቸው ለካ እንደዛ አድርጎ የደበደባቸው እሱ እንደሆነ አውቀው ኖሮ “ምን እባክህ ሐድጎ አንድ ክፉ አህያ አለኝ እሱ ክፉኛ እረግጦኝ ነው እንዲህ ተጎድቸ ለአልጋ የበቃሁት” ሲሉት ቦግ ብሎ ተነሥቶ እየነደደ ቆሽቱ እያረረ ወጥቶ ሔደ።

እሳቸው ግን ከአልጋ ከተነሡም በኋላ ጭራሽ ብሶባቸው መውጫ መግቢያ አሳጡት። ዐፄ ቴዎድሮስም እንደ በረቱበት ሰምተው አባ ገብረሐናን ተጠርተው እንዲቀርቡ አደረጉና ያ የበገነ አገልጋያቸው አንጀቱን ያርስ ብለው አባ ገብረሐና ሽምገል ከማለታቸውና ሐድጎ ደግሞ ጎረምሳ ከመሆኑ  የተነሣ እንደሚያሸንፉቸው በመተማመን ዐፄ ቴዎድሮስ “አባ ገብረሐና” ብለው ተጣሩና “በሉ እንግዲህ ምላሱ ይቅርና ታግላቹህ ይዋጣላቹህ ወንዱ ይለይ!” ብለው ዐዘዙ። አባ ገብረሐናም “አይ! አይሆንልኝም አልችልም!” እንዳይሉ **1** ኛ. ወደዱም ጠሉ የንጉሥ ትዕዛዝ በመሆኑ የማይቀርላቸው ነገር መሆኑን በመረዳት **2** ኛ. በተለያየ አጋጣሚ በእርሳቸው ተረብ የቆሰሉ በዙሪያቸው ያሉ በአባ ገብረሐና ላይ አንዳች ነገር አግኝተውባቸው በተራቸው ለመሳቅና ለማፌዝ ቁጭታቸውንም ለመወጣት አጋጣሚ ይፈልጉ በነበሩት መኳንንት ዘንድ “ምላስ ብቻ! ፈሪ!” ተብዬ ስም ከሚወጣልኝና መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆን የቻልኩትን ያህል ልታገል ብለው ወሰኑና ትግሉን ግብግቡን ገጠሙ።

ትንሽ እንደታገሉ ሐድጎ አወረደና አፈረጣቸው፡፡ ወዲያው ዐፄ ቴዎድሮስ "እህስ! ለዚህ ኖሯል ያሁሉ ምላስ? ከዚህች በኋላ አህዮ ምንትስ የምትባል ቃል ብሰማ ውርድ ከራሴ!" ብለው በኃይልና በቁጣ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እየሰጡ እንዳሉ አባ ገብረሐና መለሱና "ድሮስ ቢሆን ታዲያ አህያን በርግጫ ማን ይችላታል? ርግጫ የአሕያ አይደለም እንዴ! ከአሕያ ጋር ታግዬ ላሸንፍ ኖሯል?" በማለት አሁንም ማቁሰላቸውን ማብገናቸውን በመቀጠላቸው ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ ተቆጥተው እዛው ላይ የመንግሥታቸውን የፍትሕ ጉዳይ ከፍተኛውን ሹም (ሚንስትር) ከጎንደር አባርረው እንዲሰደዱ ፈረዱባቸው፡፡

አባ ገብረሐናም ተሰደዱ፡፡ የድፍረታቸው ድፍረት ወይም የንቀታቸው ንቀት ደሞ ሲሰደዱ የት ይሰደዳሉ? ያ ሲያበግኑት ወደ ነበረው ሰው ሀገር ትግራይ ተሰደዱ፡፡ ከዚያም ለካ ወሬው ቀድሞ ተሰምቶባቸው ኖሮ የሚያያቸው ሁሉ እየተጠቋቆመ "እህ አንተማ አንድ ጊዜ አህያ አንድ ጊዜ መረገጫ ተረጋጭ የምትለን አይደለህ?" እያሉ ከታሪካቸው እንደምንረዳው የሚያዝንላቸው አጥተው ዐፄ ቴዎድሮስ ሞተው የመጀመሪያው የትግሬ ንጉሥ ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ (አንዳንዶች ትግሬ አይደሉም ኢሮብ ናቸው ይሏቸዋል) ነግሠው የእሳቸውም የፍትሕ ጉዳዮች ከፍተኛ ሹም ወይም ባለሥልጣን (ሚንስትር) እስኪሆኑ ድረስ በሕይዎታቸው ጨርሶ የማይረሱትን የረሀብና የችግር የመቆራመድና የጠኔ የፈተና ዘመን እዚያው አሳለፉ፡፡

እዚህ ላይ ዐፄ ዮሐንስ 4ኛን "የመጀመሪያው የትግሬ ንጉሥ!" ብየ ስል አክሱም ትግራይ ውስጥ መኖሩንና ትግሮችም እዚያ መገኘታቸውን ብቻ በማየት የአክሱም ሥርዎ መንግሥት የትግሬ የሚመስለው ሰው "እንዴት?" ማለቱ የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ታሪክ የሚያውቁ የሚመስሉ ሰዎችን ጨምሮ ስንት ሰው ይሳሳታል መሰላቹህ! አሁን ላይ ትግሮቹ እዚያ መገኘታቸው እያሳሳታቸው ትግሮቹን አክሱማዊያን እንደሆኑ እያሰቡ የሥነኪን (በዘልማድ የኪነጥበብን) ሥራዎች ጨምሮ በዚህ የተሳሳተ ግንዛቤ መሠረት ተቃኝተው የተሠሩ ስንት የተሳሳተ ሥራ አለ መሰላቹህ! ነገር ግን ትግሬንና አክሱምን ምንም የሚያገናኛቸው ነገር የለም፡፡

የአክሱም ነገሥታትን ስሞች ያያቹህ እንደሆነ እንደ ዕብራይስትጥ ጽርእ የባዕድ ቋንቋ ስም ያለው ካልሆነ በስተቀር ወይ ግእዝ ነው ወይ ደግሞ አማርኛ ነው እንጅ ትግርኛ ስም ያለው አንድም ንጉሥ የለም፡፡ ያ አካባቢ ትግሬ ወይም ትግራይ የተባለውም በ4ኛው መቶ ክ/ዘ በትንሹ ከአንድ ሽህ ሦስት መቶ ዓመታት በላይ በሀገሪቱ የቆየ የነበረውን አይሁድነት ትተው ክርስትናን መቀበላቸውንና ብሔራዊ ሃይማኖት አድርገው ማወጃቸውን ተከትሎ ከአይሁዶች ጋር በተፈጠረ አለመግባባት እስከ ዘጠነኛው መቶ ክ/ዘ (እስከ ዮዲት ጉዲት) ድረስ ሲቆራቆሱ ቆይተው በጉዲት ዘመን ግን በአሸናፊነት ወጥተው በአማራው (በክርስቲያኑ) ማለትም በአክሱማዊያኑ (በሀገራችን ክርስቲያን የሚለው አጠራር በሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ዘንድ ነው እንጅ በሕዝቡ ዘንድ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አሁንም ቢሆን አይታወቅም፡፡ ብሔረሰቡ ምንም ይሁን ክርስቲያን ነኝ ለማለት አማራ ነኝ ነው የሚባለው፡፡ የሄም የሆነው ያለ ምክንያት አይደለም ክርስትናን ተቀብለው ብሔራዊ ሃይማኖት አድርገው ያወጁት አክሱማዊያን አማሮች ስለነበሩ ነው ሃይማኖቱ በእነሱ ስም ለመጠራት የበቃው)

እናም አይሁዶቹ እነ ጉዲት መቅሰፍት አውርደው አማራን (ክርስቲያኑን) ወይም አክሱማዊያኑን ከአክሱምና አካባቢዋ ስታጣፉና አማሮች (ክርስቲያኖች) ወይም አክሱማዊያን ለስደት፤ መሰደድ ያልቻሉት ደግሞ ከጉዲት መቅሰፍት እራሳቸውን ለማዳን ማንነታቸውን ከአማራነት በወቅቱ ጭቁን ወደ ሆነው ወደ ትግሬ በመቀየርና "ትግሬ ነኝ አማራ

አይደለሁም!” በማለት መትረፍ ቢችሉም የዮዲት ጉዲት ወረራ ለአርባ ዓመታት የቆየ ስለነበረ አማራውን (አክሱማዊያኑን) ከዚያ አካባቢ አጥፍቷቸው ቀረ፡፡

ጥቂቶቹ አማሮች ወደ አክሱም በመመለስ ከዮዲት በኋላ ተመልሰው የወደቀውን መንግሥታቸውን ለማንሣት ለሠላሳ ዓመታት ጥረት ቢያደርጉም ከዚያ ዘመን በፊት ንግሥናው ለእኔ ይገባል ለኔ በመባላል እየተናቆቁ የተሸነፈው ክፍል ግብጽ እየሔደ ይኖር ስለነበር ላሊበላ (እኔ ግን ላሊበላ አይመስለኝም ወይም ደግሞ በዛጉዌ ሥርዎ መንግሥት ሁለት ላሊበላዎች ነበሩ ማለት ነው) እነዚህን ያኮረፉ ስደተኛ አክሱማዊያን አግባብቶ በማምጣትና የወደቀውን የአክሱም መንግሥት ለማንሣት ይታትሩ የነበሩትን አክሱማዊያን ወግቶ ድል በማድረግ የዛጉዌን ሥርዎ መንግሥት መሠረተ፡፡ ለአማሮች ከፍተኛ ሥልጣን በማጋራት አስቀድሞ የአክሱማዊያን የምሥጢር ቋንቋ የነበረው አማርኛም ብሔራዊ ቋንቋ አድርጎ አወጀ፡፡

ከዚህ ሁሉ በኋላ ነው ያ አካባቢ በተፈጠረው አጋጣሚ ሀገራቸው አድርገውት በቀሩት ትግሮች ትግሬ ወይም ትግራይ ተብሎ የተጠራው፡፡ ትግሮች ወደዚህች ሀገር የገቡት በዐፄ ካሌብ ዘመን በምርኮ አደቡብ ዓረቢያ በአሁኑ አጠራር ከየመን ነው፡፡ ከገቡ ጊዜ ጀምሮ እንዲያገለግሉ በምርኮ እንደመግባታቸው የባርያ ሥራ ነበር እንዲሠሩ ሲደረጉ የነበሩት፡፡ ኑሯቸውም እንደባርነታቸው ነበር፡፡ ትግሬ የሚለው ስም የወጣላቸውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡

ከጊዜ ብዛትና እንዲሁም ተገደው የቀየሯቸው ነገሮች ቢኖሩም አሁንም ድረስ ግን ባሕላቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ ወጋቸውን፣ ሰብእናቸውን፣ ማንነታቸውን የተመለከትን እንደሆነ ከየመኖች ወይም ከዓረቦች ጋራ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ይበዛ ፡፡ የለቅሶና ኃዘን የሚያወጡበትን ባሕላቸውን ያየን እንደሆነ ከዓረቦቹ ጋር አንድ ነው፣ በደስታና በዓል በሚያከብሩበት ወቅት እንደ ዓረቦች ፈንዲሻ ይበትናሉ፣ ጠባያቸውን ያየን እንደሆነ ከዓረቦች ጋር አንድ ነው፣ ሴቶቻቸውን ያየን እንደሆነ እንሶስላ አዘውትሮ መሞቅን ወይም መቀባትን ጨምሮ ለጌጣጌጥ ያላቸው ፍቅርና የጌጥ አጠቃቀም ስልታቸው ከዓረቦች ጋር አንድ ነው፡፡

ወደ ቋንቋቸው ስንሔድ ትግርኛ ከሌሎች ሴማዊ የሀገራችን ቋንቋዎች በጣም በተለየ መልኩ ዓረብኛ ቃላት ይበዙበታል፡፡ የድምፅ አወጣጣቸውም እንዲሁ ሀገራችን ውስጥ ካሉ ከሌሎች ሴማዊ ቋንቋዎች የሌሉ በዓረብኛ ላይ ግን ያሉ የሰርንና የላንቃ ድምፆችን የያዘ ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በሌሎች ሀገራችን ውስጥ ካሉ ሴማዊ ቋንቋዎች ያሉ ድምፆችን በዓረብኛ ግን የሌሉትን ትግርኛም አልያዛቸውም፡፡ እነኝህ ጉዳዮች የሚያመለክቱት ወይም የሚያረጋግጡት እውነታ ምንድን ነው በዐፄ ካሌብ ዘመን በግዞት እንደመምጣታቸው ትግሮቹ ከሀገራችንና ከሕዝቧ ጋር ያላቸው ትስስር የረዘመና የጠለቀ የጠበቀ አለመሆኑን እንግዶች መሆናቸውን ነው፡፡

አማርኛን የወሰድን እንደሆነ ሴማዊ ነው ሲሉት ኩሻዊ መሠረት ያለው ሆኖ ይገኛል ኩሻዊ ነው ሲሉት ደግሞ ሴማዊ መለያም ይዞ ይገኛል፡፡ ረጅም ጊዜን ስለሚወስድ ነው ማብራሪያቱን ትቸ ነጥብ ነጥቡን ብቻ እየጠቆምኩ የማልፈው፡፡

ትግሮቹን ቀረብ ብላቹህ ስታጤኗቸው የመናዊነታቸውን የሚገልጹ ሌሎች ብዙ ነገሮችም ታገኛላቹህ፡፡ ለጊዜው ይሄ ይብቃ፡፡ ጋዳፊ እንደተናገረው ሙቱ ጠቅላይ ሚንስትር አቶ መለስ ዜናዊ ለጋዳፊ “የመናዊ ነኝ!” ብሎ የነበረው ይሄንን ታሪኩን ጠንቅቆ ከማወቁ የተነሣ ነው፡፡

ወደ አባገብረ ሐና ጉዳይ ስንመለስ አባ ገብረሐና በዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ሞገሥ አግኝተው ለዚያ ሥልጣን ይብቁ እንጂ ሕዝቡ ግን የያዘባቸውን ቂም ጨርሶ ሊረሳላቸው አልቻለም ነበር፡፡ ከሳቸውም በኋላ የሳቸውን ማለትም የአባ ገብረሐናን ስድብ ይዘው ሌሎች ሰዎችም ትግሮችን ልክ አባ ገብረሐና ሐድጎን ይሉት በነበረው መጣራትና መዝለፍ በመቀጠላቸው ትግሮቹ እንዲህ ዓይነት እንደ መርግ የሚከብድ አዋራጅና ሰብእናን የሚነካ የሚሰብር የስድብ ሸክም የጫኑበትን ሰው አባ ገብረሐናን ታሪካቸውን ከማጠጠልሸት ጀምሮ በተለያዩ መንገድ ከመበቀልም አልፈው የሳቸውን ዘር (አማራን) ባጠቃላይ አህያ እያለ እሳቸው በሰደቡት ስድብ መልሶ በመስደብ ቂሙን ለመበቀል፣ ይህ ስድብ ምን ያህል እንደሚያም ለማሳየት ጥረት ማድረግ ያዙ፡፡ ሥራዬ ብለውም ለልጆቻቸው አማራን ሲሰድቡ አድግ (አህያ) ብለው እንዲሰድቡም ያስጠናሉ፡፡

በእርግጥ አባ ገብረሐና እንዲህ ይሉ እንደነበር የሚታወቅ የተመዘገበ በመሆኑ ይህ "አህያ ተረጋጭ መረገጫ" የሚለው ስድብ በሳቸው ተጀመረ ልበል እንጅ ጉዳዩ ከትግሮቹ ለግዞት በምርኮ ከመምጣታቸው ጋር የተያያዘ ከመሆኑ የተነሣ ይሄ ስድብ ከአባ ገብረሐናም በፊት የነበረ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡

ይሁንና የአንድን ብሔረሰብ ተወላጆች እንደዚህ ወይም እንደዚያ ብሎ የዚያ ብሔረሰብ ተወላጆች በመሆናቸው ብቻ በሳደብ በእውነት ሊወገዝ የሚገባው ነውረኛ ተግባር ነው፡፡ ነገር ግን የሆነ ግለሰብን ወይም ቡድንን ከሚፈጽመው ነውረኛ ተግባር ከአስተሳሰቡ አኳያ "አህያ" ተብሎ መሰደብ ቢኖርበት ማን ነው ይሄ ስድብ የሚገባው? የሚገልጸው? የሚስማማው? ካልን ይሄንን ለመበየን በቅድሚያ የአህያን ማንነት መፈተሽ ይኖርብናልና እስኪ አህያ ማን ናት? ምንስ ትመስላለች? መገለጫዎቿ ምን ምን ናቸው? የሚለውን እንይ፡-

ሁላችንም እንደምናውቃት አህያ ከጋማ ከብቶች አንዷ እንደመሆኗ ለሸክም እንደተፈጠረችና ለምን እንደሆነ ባይታወቅም የተናቀች ክብርም የሌላት እንስሳ ናት፡፡ አህያ የሰውን ልጅ በሸክም እጅግ በጣም ታግዛለች፡፡ የቱንም ያህል ክብደት ይኑረው የመጨረሻ አቅሟ በፈቀደላት መጠን የጫኗትን ሁሉ በመጫን ጌቶቿን ታገለግላለች፡፡

አህያ ራቅ ያለውን ማየት የማትችል የጥቂት እርምጃዎችን ርቀት ያህል ብቻ የመመልከት ደካማ የማየት ዐቅም ያላት አርቃ ማየት የማትችል፤ ጆሮዋ ግን እጅግ በሚገርም ሁኔታ የሩቅና ከየአቅጣጫው ያለውን ኮሽታም እንኳ ሳይቀር መስማት የምትችል ከዛም አልፋ ጨርሶ ለመስማት የማይቻለውን ከደመና በላይ ያለውን ቅድመ ዝናብ ዝግጅት ዝናብ የመምጫ ምልክቶችን የመስማትና እራሷን የማዘጋጀት አስደናቂ የመስማት ችሎታ ያላት እንስሳ ነች፡፡

ከዚህ ውጭ ግን በተለይ ሆዷ እስከሞላላት ድረስ ማንም ምንም ይጫናት ምን? ለምን ነው የምጫነው? እንዴት? እምቢ አልጫንም! የሚባል የሞራል (የቅስም) እና የሙብት ጥያቄ የማይሰማት፣ የማታነሣ፣ የመጫን ሱስ ያለባት፣ ካልተጫነች ካልተገጠበች ጥጋብ የማይስማማት አሳውሮ ገደል የሚወረውራት ምስኪን እንስሳ ናት፡፡

በመሆኑም "አህያ" የሚባለው ስም ወይም ስድብ የሚስማማው፣ የሚገልጸው ሰው ወይም ቡድን የአስተሳሰቡ መሠረት "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይበቀል!" ለሆነውና የሀገርን ጥቅም በግል ጥቅም ለሚለውጠው፣ የግል ጥቅሙን ለማስጠበቅ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ጠላቶች ለባዕዳን በባንዳነት አድሮ አገልጋይ ሆኖ በሀገራችንና በሕዝባችን ዕጣ ፋንታ ላይ ለሚቆምረው፣ ለግል ጥቅሙ ሲል ጥቅማችንን አሳልፎ ለሚሰጠው፣ እምቢ ለክብሬ ለማያውቀው፣ የሀገርና የሕዝብ ጥቅም ብሎ ነገር የማይገባው፣ ማንነት ክብር ነፃነት ሳይል እንደ እንስሳ ሆዱን ብቻ በማሰብ ሆዱን እስከሞሉለት ጊዜ ድረስ የጫኑትን

ሁሉ ለሚጫን ያሸከሙትን ሁሉ ለሚሸከም፣ ባርነትን አሜን ብሎ ተቀብሎ ፋሽስት ጣሊያን እንደፈለገ እንዳሻው ሲገጥበው የኖረው አሁንም የእነሱን የጌቶቹን ጥቅምና ዓላማ ለማስፈጸምና ለማስጠበቅ ሀገርና ሕዝብን ለሚያውከው፣ የሚያኮራውንና የሚያሳፍረውን መለየት ለማይችለው፣ የማንነት፣ የክብር፣ የነጻነት፣ የሀገር፣ የድንበር፣ የታሪክ ነገር የማይገደው የማይሰማውና ማይገባው፣ በፍርፋሪውም በምኑም የሚደልሉት እንስሳዊ ባሕርይ ያለው የባዕድ ወይም ለጠላት ባሪያ አገልጋይ ባንዳ ነው **"**አህያ**"** የሚባለው እሽ**?**

እንጅ እምቢ ለነፃነቴ፣ እምቢ ለማንነቴ፣ እምቢ ለክብሬ፣ እምቢ ለሀገሬ፣ እምቢ ለድንበሬ ለሚለው፤ ከራሱ ግላዊ ወይም ቡድናዊ ጥቅሞች ይልቅ ለሀገሩ፣ ለማንነቱ፣ ለክብሩ፣ ለነፃነቱ፣ ለታሪኩ ለድንበሩ ቀናዒ ለሆነና የእነዚህ ሀብቶቹ እሴቶቹ ነገር ለሚከነክነው ለሚያንገበግበው ዕረፍት ለሚነሳውና አንድያ ነፍሱን ለእነዚህ እሴቶቹ ለሚሰጠው ባለ አደራነት ለሚሰማው ተዋርዶ ከመጥገብ ይልቅ ተርቦ መኩራትን ለሚመርጠው፣ የሀገሩን ጥቅም በግል ወይንም በቡድን ጥቅም ለውጦ የጠላት አገልጋይ ከመሆንና ሀገሩን ከመሸጥ ሸህ ሞትን ለሚመርጠው የሰብአዊ ባሕርይ መገለጫ ለያዘው ነፃና ኩሩ ዜጋ፣ ኩራት እራቴ ለሚለው የሀገር ልጅ አይደለም**!!!** ይሄንን መለየት አለመቻላቸውም ነው ከአህያነት ለመለየት ለመውጣት እንዳይችሉ ያደረጋቸው፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ**!!!** ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር**!!!**

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

**amsalugkidan@gmail.com**

***http://www.ethiopanorama.com***